ቀን 4/03/2011ዓ.ም

ኮሚኒኬ ቁ. 006/11

# ኢ.መ.ድ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባዘጋጀው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ተሳተፈ

ኢ.መ.ድ ከጥቅምት 22 እስከ 26 ቀን 2011 ዓ.ም የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአዲስ አበባ ኤግዚሽን ማዕከል ባዘጋጀው 11[ኛው] ኢትዮ ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ተሳተፈ፡፡

ኤግዚቢሽኑ ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት አካባቢ የንግድ ሚኒስቴርና የኢ.መ.ድ የሥራ አመራር ቦርድ አባል ክብርት ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገ/እግዚአብሔር በተገኙበት ተከፍቷል፡፡



የኤግዚቢሽኑ ገፅታ በከፊል

ለአምስት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ የቆየው ይህ የንግድ ትርዒት “የኢትዮጵያን ይግዙ” በሚል መሪ ቃል የተካሄደ ሲሆን አብዛኛዎቹ ተሳታፊ ሆነው የቀረቡት ድርጅቶችም ሀገር ውስጥ አምርተው ለውጪ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም በተሠጠው ማሳያ ቦታ ላይ በተለያዩ ባነሮች በመታገዝ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ ስላስመዘገባቸው ውጤቶች (በአረቦን ገቢ፣ የካሳ ክፍያ፣ የኢንቨስመንት፣ ትርፍ…ወዘተ) ለማሳየት የቻለ ሲሆን እንዲሁም በቴሌቪዥን በመታገዝ የድርጅቱ ምርትና አገልግሎቶች እንዲተዋወቁ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የዋስትና አይነቶች ዙሪያ የተዘጋጁ ብሮሸሮችን በመጠቀም ለጎቢኚዎች በማስረዳትና በማሰራጨት ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት የተደረገ ሲሆን የተለያዩ የመድን ዋስትናዎችን ለመግዛት ለሚፈልጉ ጎብኚዎች ሰፊ ማብራሪያ መስጠት ወደሚችሉትና አገልግሎቱቹን በአቅራቢያቸው ወደሚሰጡት የድርጅቱ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች ጎራ እንዲሉ ተገልፆላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ 11[ኛው] ኢትዮ-ቻምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርዒት አዳዲስ ደንበኞችን ለማፍራትና ለነባር ደንበኞችም በቅርቡ ገበያ ላይ የዋሉ አዳዲስ ምርቶችን (policies) እና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ሠፊ እገዛ እንደነበረው የታመነበት ሲሆን መስተካከል የሚገባቸው ተብለው በጎብኚዎች የተነሱ አስተያየቶች ላይ ግብረ መልስ (feed back) ለመውሰድ ተችሏል፡፡